VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH

# Mpox

## ስለ mpox

Mpox በMpox ቫይረስ የሚፈጠር ሽፍታን የሚያስከትል ተላላፊ በሽታ ነው Mpox የተለያዩ ምልክቶች አሉት  አንዳንድ ሰዎች ቀለል ያሉ ምልክቶች ሲያሳዩ ሌሎች ደግሞ ከባድ ምልክቶች ያሳያሉ እና በጤና እንክብካቤ ተቋም ውስጥ እንክብካቤ ማግኘትያስፈልጋቸዋል። እርጉዝ ሴቶች፣ ህጻናት እና የበሽታ መከላከል አቅማቸው የተዳከመ ሰዎች ለከባድ ሕመም እና ለዉስብስብ የጤና ችግሮች ተጋላጭ ናቸው።

የmpox ቫይረስ ሁለት ዓይነቶች ናቸው፦ ምድብ I እና ምድብ II።

- ምድብ II በ2022 የጀመረውን ዓለም አቀፍ ወረርሺኝ የከሰተው ዓይነት ሲሆን ቨርጂኒያን ጨምሮ አሜሪካ ውስጥ ታካሚዎች በዝቅተኛ መጠን ሪፖርት መደረጋቸውን ቀጥለዋል።
- ምድብ I ከ2023 ጀምሮ በማዕከላዊ እና በምርራቅ አፍሪካ የታካሚዎችንቁቁጥር እየጨመረ የሚገኘው ዓይነት ነው። ምድብ I ከምድን II ይልቅ በቀላሉ ይሰራጫል እና በታሪክ ይበልጥ አደገና በሽታ እና ሞትን አስከትሏል። ከኦገስት 2024 ጀምሮ፣ ምድብ I ከአፍሪካ ውጪ ሪፖርት ተደርጓል። በአሜሪካ የተገኘው የመጀመሪያው የምድብ I ታካሚ ኖቬምበር 2024፣ ካሊፎርኒያ ውስጥ ነበር።

## mpox እንዴት እንደሚሰራጭ

ሰዎች በmpox ከተያዘ ሰው ጋር በቅርብ ግንኙነት ላይ ከሆኑ mpox ሊይዛቸው ይችላል። ስርጭት የቆዳ ቁስል፣ የሰውነት ፈሳሾች ወይም ከተጠቃ ሰው ጋር ንክኪ የነበራቸውን አልባሳት ወይም አንሶላዎች ከመንካት ሊከሰት ይችላል። እንዲሁም ስርጭት በተራዘመ የፊት-ለፊት ግንኙነት ወቅት ሊከሰት ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ምልክታቸው ከመጀመሩ ከአንድ እስከ አራት ቀናት በፊት mpoxን ወደ ሌሎች ሊያሰራጩ ይችላሉ።

Mpox ከሰው ወደ ሰው በሚከተሉት መንገዶች **ሊሰራጭ ይችላል**፦

- ወሲባዊ ወይም ስሜታዊ ግንኙነት (የአፍ፣ የፊንጢጣ እና የብልት ወሲብን ጨምሮ)
- መተቃቀፍ፣ መሳሳም፣ መላፋት እና ማሰጅ
- አልጋ፣ ያልታጠበ ፎጣ ወይም አልባሳት መጋራት

Mpox በሚከተሉት መንገዶች ከሰው ወደ ሰው **አይሰራጭም**

- ከተጠቃ ሰው ጋር ውይይት ማድረግ
- በተጠቃው ሰው አጠገብ ማለፍ



*የፎቶ ምስጋና፦ የዩኬ የጤና ደህንነት ኤጀንሲ*

## የmpox ምልክቶች

በማንኛውም የሰውነትዎ ክፍል ላይ የቆዳ ሽፍታ (1 ወይም 2 ነጥቦች ቢሆንም እንኳን)። ለአንዳንድ ሰዎች፣ ይህ ሽፍታ ብቸኛ ምልክታቸው ሊሆን ይችላል። ሌሎች ምልክቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- ትኩሳት
- መንቀጥቀጥ
- ራስ ምታት
- የጡንቻ ህመም እና የጀርባ ህመም
- ያበጡ ንፍፊቶች
- የድካም ስሜት
- የመተንፈሻ አካላት ምልክቶች (የአፍንጫ መደፈን፣ ሳል ወይም የጉሮሮ ህመም)

ሁሉም ወይም ጥቂት ምልክቶች ሊኖሩዎት ይችላሉ። ምልክቶች በአብዛኛው ከመጋለጥ 3 ሳምንታት በኋላ ይታያሉ።

VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH

## የmpox ምልክቶች ካሉዎት ምን ማድረግ እንዳለብዎት

ምልክቶች ካሉዎት፣ ራስዎን ከሌሎች ሰዎች እና የቤት እንስሳት መለየት፣ ሽፍታዎን መሸፈን እና የእርስዎን የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ማነጋገር አለብዎት።

ወደ የጤና እንክብካቤ ተቋም ከመሄድዎ በፊት ስለ mpox ስጋት እንዳደረብዎት ደውሎ መናገር አስፈላጊ ነው።

ከእርስዎ አቅራቢ ጋር ከመነጋገርዎ በፊት ከሌሎች ጋር ቅርብ አካላዊ ግንኙነትን ማስቀረት አለብዎት።

## mpoxን እንዴት መከላከል እንደሚቻል

**ክትባት ይውሰዱ።** ባለ-ሁለት ክፍሉ የmpox ክትባት mpox ካለበት ሰው ጋር የሚታወቅ ተጋላጭነት ለነበራቸው ወይም ከፍተኛ የተጋላጭነት አደጋ ላይ ለሆኑ ሰዎች ይመከራል። ለከፍተኛ ጥበቃ፣ የክትባቱን ሁለቱንም ክፍል መውሰድ አስፈላጊ ነው። ለክትባት ብቁ መሆንዎን ለመመልከት የCDC mpox ድረ-ገጽ ይጎብኙ። ክትባት ለመውሰድ የእርስዎን የአካባቢ የጤና ክፍል ያነጋግሩ..

ከሌላ ሰው ሽፍቶች ወይም የቁስል ቅርፊቶች ጋር ቅርብ፣ የቆዳ ለቆዳ ንክኪ ከማድረግ ይቆጠቡ። ከተጠቃ ሰው ጋር ከመሳሳም፣ ከመተቃቀፍ፣ ከመላፋት ወይም ወሲብ ከመፈጸም ይቆጠቡ። የመመገቢያ መሣሪያዎችን እና ኩባያዎችን አያጋሩ። አልጋ ልብስ፣ ፎጣዎች ወይም የግል ንጽህና መጠበቂያ መሳሪያዎችን አያጋሩ።

ከተጠቁ ግለሰቦች ጋር ንክኪ ከነበረዎት በኋላ እጆችዎን በሳሙና እና በውሃ **ይታጠቡ** ወይም የአልኮል የእጅ መታጠቢያ ይጠቀሙ።

mpox እንዳለብዎት ካሰቡ እና ከሌሎች ሰዎች ጋር የፊት ለፊት ግንኙነት ማድረግ ካለብዎት ወይም ተጠቅቶ ሊሆን ከሚችል ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት ማድረግ ካለብዎት፣ የፊት ጭንብል **ያድርጉ**።

የሚታደሙባቸውን ዝግጅቶች እና በእነዚያ ዝግጅቶች ላይ የሚኖርዎትን ባህሪ **ከግምት ውስጥ ያስገቡ።** ቅርብ፣ የተራዘመ የቆዳ ለቆዳ ንክኪ ካለ mpoxን የማሰራጨት እድል ከፍተኛ ነው።

## የmpox ህክምና

የተዳከመ በሽታ የመከላከያ ሥርዓቶች እንዳሏቸው ሰዎች በከፍተኛ ሁኔታ የመታመም እድል ላላቸው ሰዎች እንደ ቴኮቪሪማት (TPOXX) ያሉ ጸረ-ቫይረሶች ሊመከሩ ይችላሉ።

ስለ ህክምና ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ ወይም የቴኮቪሪማት (TPOXX) ጥናት ለMpox (STOMP) ሙከራ የሚለውን ይመልከቱ ይህም ነጻ ህክምናን ያቀርባል እና ሰዎች በርቀት ሙከራው ላይ መሳተፍ ይችላሉ።

እንዲሁም mpox የተገኘባቸው ሰዎች እንደ ህመም፣ ማሳከክ፣ ማቅለሽለሽ እና ማስመለስ ላሉ ምልክቶች ህክምና ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

## ስለ mpox የበለጠ መረጃ ለማግኘት

የVDH ድረ ጣቢያን vdh.virginia.gov/mpox ላይ ይጎብኙ

ኦክቶበር 2024